## ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

### ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ኤሌክትሪክ- ከከተሞች እድገት ጀርባ

ኢያሱ መሰለ

ለአንድ ሀገር እድገትና ብልጽግና ፣ ለሕዝቦች ሥልጣኔ እና ዘመናዊ አኗኗር ጉልህ አስተዋጽኦ ከሚያበረክቱ ጉዳዮች ውስጥ ኤሌክትሪክ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። ከተሞች የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ከመሆናቸው በፊት እና በኋላ የሚኖራቸው ገጽታ በእጅጉ ይለያያል። ኤሌክትሪክ ለከተሞች ድምቀትን የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ኢንዱስትሪዎች ምርታማ እንዲሆኑ፣ ሆቴሎችና ተቋማት የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ፤ የንግድ ሥራዎች እንዲሳለጡ የሚያስችል ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ በርካታ የሀገራችንን ከተሞች መጥቀስ ይቻላል።

የስልጤ ዞን የማንነት ጥያቄው ከተመለሰለት ከ1995 ዓ.ም በኋላ የወራቤ ከተማን ዋና መቀመጫው አድርጎ በአዲስ መልክ መዋቅራዊ አደረጃጀት አድርጓል። ይህንን ተከትሎም የዞኑ ተወላጆች አካባቢያቸውን እንዲያለሙ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ወራቤ እያደጉ ካሉ የሀገራችን ከተሞች መካከል አንዷ ለመሆን በቅታለች። ከእድገቷ ጀርባ ያለው ትልቁ ሞተር ደግሞ ኤሌክትሪክ ነው። የወራቤ ከተማ አስተዳደር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በመነጋገር የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቷን አሟልቶ ለአልሚዎች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ከተማዋ ፈጣን እድገት እንድታስመዘግብ መደላድል ፈጥሯል። ዛሬ የወራቤ ከተማ በርካታ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታልን ጨምሮ የጤና ተቋማትና ዩኒቨርሲቲ ተፈጥረውበታል። ከዚህ ሁሉ ለውጥ ጀርባ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ አቶ ያሲን ከሊል የወራቤ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ያስረዳሉ።

ከተማዋን ለማሳደግ ሲታሰብ የመጀመሪያው ርምጃ የልማት ማህበር ማቋቋም እንደነበር የገለጹት ከንቲባው ማህበሩ በተለያዩ ሀገሮች የሚገኙ የአካባቢው ተወላጆች አካባቢያቸውን እንዲያለሙ ጥሪ የማቅረብ ሥራ ሲያደርግ አስተዳደሩ በበኩሉ ከተማዋን ለአልሚዎች ምቹ የማድረግ ሥራዎችን አከናውኗል። በዚህ የተነሳ ወራቤ ከተማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ መሻሻልና እድገት አሳይታለች።

ከተማዋ የዞኑ ማዕከል ሆና ስትቋቋም ለእድገቷ ማነቆ ይሆናሉ ተብለው ስጋት ከፈጠሩ ጉዳዮች አንዱ የኃይል አቅርቦት እጥረት ነበር። ከተማዋ ቀደም ሲል ኃይል የምታገኘው ከጀኔሬተር እንደሆነ የጠቀሱት ከንቲባው የከተማዋ የመልማት አቅም ሲያድግ ከቡታጅራ ሰብሲቴሽን ኃይል በመሳብ ለልማት ሥራው ማዋል እንደተቻለ ጠቅሰዋል። ያም ሆኖ የኃይል አቅርቦቱ ከከተማው እድገት የሚመጣጠን አልነበረም፤ በዚህም ላይ የኃይል መቆራረጥ ይስተዋል ነበር። አሁን ግን በወራቤ ከተማ የተገነባው ሰብስቴሽን ለከተማዋና ለአካባቢው እድገት ትልቅ እድል ፈጥሯል። ከተማ አስተዳደሩም የኃይል አቅርቦቱን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የእቅዱ አካል አድርጎ እየሠራ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል። ወራቤ ከተማ ከ 15 ሺህ በላይ ካሬ ስፋት እንዳለው የጠቀሱት አቶ ያሲን በከተማው የኢንዱስትሪ ዞን፣ የሆቴል ፣ የኢንተርፕራይዝ ቦታዎችን በመለየት የማልማት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በኢንዱስትሪው መንደር 147 የሚሆኑ ለማኑፋክቸሪንግ የተሰጡ ቦታዎች እንዳሉ ጠቅሰው የኤሌክትሪክ እጥረት አልሚዎቹ ወደ ሥራ ሳይገቡ ቦታውን ብቻ ወስደው ለረዥም ጊዜ ያለሥራ እንዲቀመጡ አድርጓቸው ነበር ይላሉ። የወራቤ ሰብስቴሽን ሥራ ከጀመረ አንስቶ አብዛኛዎቹ ባለሀብቶች ፈጥነው ወደ ሥራ መግባት ችለዋል። የሰብስቴሽኑን መገንባት ተከትሎም አሁንም በርካታ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች እየተተከሉ እንዳሉና የሰዎች ወደ ከተማዋ መጥቶ የመኖርም ሆነ የማልማትም ፍላጎታቸው እየጨመረ መምጣቱን ተናግረዋል።

የሰብስቴሽን ጥያቄው ለአጠቃላይ የስልጤ ማህበረሰብ እንጂ ለወራቤ ከተማ ብቻ አልበነረም ያሉት አቶ ያሲን በጥያቄው መሠረት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መልስ በመስጠቱ በዞኑ የሚገኙ ከተሞች ተስፋቸው ለምልሟል ይላሉ።

ተቋሙ ለሰብስቴሽን መገንቢያ በመረጠው ቦታ 17 የሚሆኑ መኖሪያ ቤቶች እንደነበሩ ጠቅሰው ነዋሪዎቹ የልማት ተነሺዎች በሚስተናገድበት አሠራር መሠረት ምትክ የከተማ ቦታ እንዲያገኙ መደረጉንና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልም አስፈላጊውን የካሳ ክፍያ እንዳደረገላቸው ገልጸዋል፤ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለእያንዳንዱ የልማት ተነሺ አባ እና እማ ወራ መቋቋሚያ እንዲሆናቸው የወተት ላሞችንም አበርክቷል።

ሰብስቴሽኑ በአሁኑ ጊዜ በአራት መስመሮች ወደ ኢንዱስትሪ መንደሮቹ ኃይል ለማሰራጨት በዝግጅት ላይ ያለ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል። ከተማ አስተዳደሩም በ2017 በጀት ዓመት ወደ ኢንዱስትሪ መንደሮቹ ኃይል ለማስገባት በጀት አጽድቆ ለቀጣይ ሥራዎች ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል። በአሁኑ ሰዓት 16 የሚሆኑ ፋብሪካዎች ማሽን ገጥመው መብራት በመጠባበቅ ላይ እንዳሉም ገልጸዋል።

በተለይም ከለውጡ ወዲህ ባለሀብቶች ወራቤ ላይ ኢንቨስት የማድረግ ፍላጎት እንዳሳዩ የተናገሩት ከንቲባው በከተማው እስከ አሁን 760 ሄክታር መሬት ለኢንቨስትመንት ዝግጁ ሆኖ አብዛኛው ሥራ ላይ ሲውል ከዚህ ውስጥ 80 ሄክታር መሬት አሁንም አልሚዎችን እየጠበቀ ነው ብለዋል።

አሁንም ባለሀብቶች መጥተው ቢያለሙ አስተማማኝ የመብራት አቅርቦት እንደሚያገኙና ከሰላም አንጻርም ስጋት እንደማይገጥማቸው ገልጸዋል።

ወራቤ እንደሀገር ተስፋ የተጣለባት አዳጊ ከተማ



አቶ ያሲን ከሊል

ነች ያሉት አቶ ያሲን በአካባቢው በፌዴራል መንግሥት እየተገነባ ያለው ግዙፍ የመስኖ ፕሮጀክት ተጠናቆ ወደ ሥራ ሲገባ ደገሞ ግብርናን ከኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር በእጅጉ የሚረዳ እንደሆነና ለዚህም የኤሌክትሪክ አቅርቦትን አስቀድሞ የማሟላቱ ሥራ አስፈላጊ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በአጠቃላይ ወራቤ ከተማ ኢንዱስትሪ ፣ ሆስፒታል፣ የምርምር ማዕከል ፣ ሆቴሎች ፣ ዩኒቨርሲቲና ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን የያዘች ነች። የኤሌክትሪክ ፍላጎቷም በዚያው ልክ እያደገ የመጣና ቀጣይ እድገቷን የሚያፋጥን እንደሆነ አብራርተዋል። በከተማው የተገነባው ሰብስቴሽንም ለከተማዋ እድገትና ልማት የጀርባ አጥንት እንደሆነ ገልጸው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከከተማዋ ሁለንተናዊ እድገት አንጻር ስላበረከተው አስተዋጽኦም አቶ ያሲን ምስጋና አቅርበዋል።